የኢትዮጵያውያን ሕዝባዊ ማህበራት ጉባኤ (ኢሕማጉ)
Congress of Ethiopian Civic Associations (CECA

# ፋኖ ተባበር፣ እንዳትሰባበር

**CECA Press Release: April 12, 2025**

የኢትዮጵያዉያን ሕዝባዊ ማኅበራት ጉባዔ (ኢሕማጉ)፤ በዲያስፖራ የሚገኝ የመብት-ተኮር ተሟጋች ማሕበራት ስብስብ፤ የዐማራ ሕዝብ ላለፉት ሁለት አመታት ተደራጅቶ በኅልውናው ላይ በዘውጌ ሃይሎች የተጋረጠበትን የማያባራ ጥቃት መክቶ በሚያስደምም ጀግንነት ሲታደግ እኛም አለንልህ ብለን ከጎኑ ቆመን ቆይተናል። በተለይም የነጻነት ንቅናቄው መነሻው የዐማራን ሕልውና ማስከበር፣ መዳረሻው ደግሞ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና በእኩልነት የተመሰረተ የሕዝቧን አንድነት ማስከበር በመሆኑ ሁሉም ኢትዮጵያዊያን ለራሳቸው ሲሉ ይህን ፍትሃዊ ትግል በተግባር እንዲደግፉ ስንጎተጉት ቆይተናል፤ አጠናክረን እንቀጥላለንም።

የፋኖ አፈጣጠር ከታች ወደ ላይ ስለሆነ ወደ መዋቅራዊ አንድነት ለመምጣት ትልቅ ተግዳሮት እንደሚገጥመው ሳይታለም የተፈታ ነው። ነገር ግን መዳረሻውና የትግሉ ፍኖተ-ካርታ እየጠራ ስለመጣና ትግሉ ወደ መጨረሻው ምዕራፍ በመድረሱ የትብብር ጥያቄ ለነገ ወደማይባልበት ደረጃ ደርሷል። ተስፋ ሰጪና ተስፋ ነሺ ክስተቶችም እየታዩ ነው።

በፈቃደኝነት ወደ አንድ አመራር ለመምጣት የተደረጉ ሙከራዎች ሁሉ ተስፋ ሰጪ ናቸው፤ ስኬታማ እስኪሆኑ ድረስ ጥረቱን በቅን ልቦና መቀጠል ግድ ይላል። ባላፉት ሶስት ሳምንታት ብቻ በመናበብ የተደረጉ ስኬታማ ድሎች የትብብርን ቁልፍ ሚና ማሳያ ትልቅ ምሣሌ ሲሆን፤ ኀጠኝነትና ፍጹማዊነት እኩይ መሰናክሎች መሆናቸውን አጋልጧል። የሚታለመው የድኅረ-ድል ዲሞክራሳዊ ሥርዓት ግንባታ ለነገ የማይባልና በትግሉ ወቅት መኮትኮት እንዳለበትም ከታሪክ እየተማርን በትብብርና በመናበብ ትግሉ እንዲመራ አደራ እንላለን።

ስለሆነም፤ ተደጋግሞ ከአራቱም ክፍለ-ሃገራት የምንሰማው መተናኮስና ለመተኳኮስ መፈላለግ፤ የሕዝባችንን የነፃነት ተስፋ እንደሚያደበዝዝ ልብ ብለን፤ ለፋኖ የማይመጥንና የትግሉን ስኬታማ ሂደት አላስፈላጊ በሆነ መናቆር ማራዘምም ይሆናል። እስካሁን ባልታየ ጭካኔ የመጨፍጨፍና የኢኮኖሚ ማዕቀብ አፋፍ ላይ ያለው የዐማራ ሕዝብም የጋራ ግንባርን ሂደት እንጂ መከፋፈልን የመቀበል አቅምም ፈቃድም እንደሌለው በመገንዘብ **“ድርጅታዊ አንድነት አንገብጋቢ ጥያቄ ነው”** በማለት አጋራዊ ምክራችንን ልንለግስ እንወዳለን።

ድል ለዐማራ ሕዝብ፤

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!